📚 #Civics and Moral Education.

📚 Chapter Two - Approaches to Ethics.

📚 Immanuel Kant - Categorical imperative Ethics.

🙌 ከ Chapter 2 የተዘለሉ ትምህርቶችችን በዚህ ትምህርት ለመዳሰስ እንሞክራለን። ካሁን በፊት በነበረው ትምህርታችን ስለ kant Ethics ተምረናል። እናስታውሰው እስኪ።

🙌 የ ጀርመናዊው ፈላስፋ Immanuel Kant Ethics ብዙ መጠሪያ ስሞች አሉት። እነርሱም👇

📌 Kantism.
📌 Kantian Ethics.
📌 Categorical imperative Ethics.
📌 Unconditional Command Ethics.
📌 Absolute Command Ethics.

🙌እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ የ Immanel Kant Ethics መጠሪያ ስሞች ናቸው።

🙌 እንግዲህ ካስታወሳችሁ ፤ Ethics በሁለት እንደሚከፈል ተምረናል። እነርሱም Normative Ethics ና Non-normative Ethics ይባላሉ። Normative Ethics ማለት የ ሰው ልጆች የሚያደርጓቸውን ድርጊቶች ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት የሚያጠና Ethics ነው ፤ ማለትም የትኞቹ

ድርጊቶች ትክክል ናቸው የትኞቹ ድርጊቶች ስህተት ናቸው የሚለውን ያጠናል ማለት ነው። ታዲያ Normative Ethics ከሞራል አንፃር የድርጊቶችን ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት ሲያጠና ፤ ድርጊቶቹ ከሚያስከትሉት ውጤት(Consequence/End) አንፃር ሊሆን ይችላል ፥ ድርጊቶቹ መደበኛ የስነ-ምግባር ደንቦችን(duty) ከማክበራቸው ወይም ካለማክበራቸው አንፃር ሊሆን ይችላል ፥ እንዲሁም ድርጊቱን ካደረገው ሰውየ ባህሪ(Virtue) አንፃር ሊሆን ይችላል።

📚 በዚህም ምክንያት Normative Ethics በ ሶስት ይከፈላል።  እነርሱም👇

📌 Teleological Ethics
📌 Deontological Ethics
📌 Virtue Ethics.

🙌 ስለ Teleological Ethics(ውጤት ተኮር Ethics ወይም Consequence based Ethics) በጣም በሰፊው ተምረናል። እዚህ ላይ መድገም አይጠበቅብንም። ስለ Deontological Ethics( duty based Ethics) ም በሰፊው ተምረናል። Deontological Ethics በአራት እንደሚከፈል ተምረናል። እነርሱም👇

📌 Divine Command Theory(DCT).
📌 Rights Theory.
📌 Immaunel Kant Categorical imperative

Ethics.
📌 Prima Facies Duty.

🙌 ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩት እነዚህ አራቱ... ድርጊቶችን ትክክል ናቸው ወይም ስህተት ናቸው ብለው የሚፈርጁት እንደ Teleological Ethics(Egoism and Utilitarianism) ድርጊቶቹ በሚያስከትሉት ውጤት(consequence/end) ሳይሆን ድርጊቶቹ ህግና ደንብን(duty/means) በማክበራቸው ወይም ባለማክበራቸው ነው። ከ አራቱ ስለ DCT ና Rights Theory ተምረናል። ዛሬ የምንማረው ስለ Kant ና Prima Facie duty ነው።

📚 **Kant's Categorical Imperative Theory.**

🙌 መጀመሪያ Imperative ማለት ምን ማለት ነው❓የሚለውን እንማር።

📌 Imperative ማለት ትዕዛዝ(Command) ማለት ነው። ትዕዛዝ ማለት ደግሞ "አድርግ ወይም አታድርግ" ማለት ነው። ለምሳሌ :- አትስረቅ ፤ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ ፤ ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ጠንክረህ አንብብ ፤ አትዋሽ ፤ ቃልህን ጠብቅ ወዘተ እነዚህ ትዕዛዝ(imperative) ናቸው።

🙌 እንደ Ethics ትምህርት አስተምህሮ ፤ ትዕዛዝ(Imperative) በሁለት ይከፈላል👇

1) Hypothetical imperative.
2) Categorical imperative.

📌 Hypothetical imperative - tell us which means best achieve our ends. They do not, however, tell us which ends we should choose.

🎯 Hypothetical imperative በሌላ ስሙ Conditional Command ተብሎ ይጠራል። ሎጂክ ትምህርት ላይ ስለ Hypothetical Syllogism ተምረናል። Hypothetical syllogism ማለት በ Conditional sentence የሚገለፅ ነው ብለናል፤ Conditional Sentence ማለት ደግሞ "if....then" ማለት ነው ፤ Conditional ማለት በሁኔታዎች የሚወሰን ማለት ነው። ለምሳሌ 👇

If you want to be rich, then You have to work hard.

👆ተመልከቱ ይህን ዐ.ነገር ፤ "ሀብታም ለመሆን ጠንክረህ መስራት አለብህ።" ከመሬት ተነስቶ ሀብታም አይኮንም ፤ ሀብታም ለመሆን የሆነ ሁኔታ(condition) ማሟላት ያስፈልጋል ፤ እርሱም ጠንክሮ መስራት ነው። ስለዚህ ሀብታም መሆን በጠንክሮ መስራት ሁኔታ ይወሰናል ማለት ነው። ስለዚህ በሁኔታዎች የሚወሰኑ ድርጊቶች Hypothetical(conditional) ይባላሉ። 😁

ስለዚህ Hypothetical imperative ማለት በሁ���ታዎች የሚወሰን ትዕዛዝ ማለት ነው - Conditional Command የተባለው ለዛ ነው። ስለዚህ Hypothetical imperative ማለት👇

📚 አንድ ነገር ለማግኘት ወይም አንድ ነገር ለመሆን ፤ ያንን ነገር ለማግኘት/ለመሆን የግዴታ ማድረግ ያሉብን ነገሮች የሚገልፅልን ትዕዛዝ Hypothetical imperative ይባላል።

😁 ለምሳሌ 👇

📌 ዩኒቨርሲቲ ለመግባት Entrance ማለፍ አለብህ(If u want to join a university, u must pass entrance).

📌 ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ጠንክረህ ማንበብ አለብህ ፤(u must study hard to be clever student.)

📌 ታሞ ለመታከም ሆስፒታል መሔድ አለብህ፤(u must go to a hospital to get treatment.)

📌 ጥሩ ገቢ ማግኘት ከፈለክ ጠንክረህ መስራት አለብህ።( If u want to have a better income, u must work hard.)

🙌እነዚህ ከላይ የተዘረ��ሩት አራቱ ምሳሌዎች Hypothetical imperative ናቸው ፤ ማለትም አንድ ነገር ለማግኘት/ለመሆን/ለማድረግ ፤ የግዴታ

ማድረግ ማሟሟላት ያሉብን ነገሮችን የሚገልፅልን ትዕዛዝ ነው። በሌላ አባባል በሁኔታዎች(conditional) የሚወሰኑ ትዕዛዞችን ይገልፅልናል።

📚 ስለዚህ አንድ ነገር ለማግኘት ብለን የግዴታ ማድረግ ያለብን ነገር hypothetical imperative ይባላል።

😎ስለዚህ ሁለት ነገሮችን እንረዳ👇

1) End - ማድረግ ወይም ማግኘት የምንፈልገው ነገር end ይባላል፤ ለምሳሌ ከላይ እንዳየነው ግቢ መግባት ፤ ጎበዝ ተማሪ መሆን ፤ መታከም ፤ ጥሩ ገቢ ማግኘት ወዘተ End ናቸው።

2) Means - End ዱን ለማግኘት የግዴታ ማድረግ ያለብን ነገር means ይባላል። ለምሳሌ ከላይ እንዳየነው Entrance ማለፍ ፤ ጠንክሮ ማጥናት ፤ ሆስፒታል መሔድ ፤ ጠንክሮ መስራት ወዘተ Means ናቸው።

🙌ስለ Hypothetical imperative ይህን ካየን በቂ ነው። Categorical imperative ን እንመልከት።

📌 Categorical imperative በሌላ ስሙ Unconditional command ወይም Absolute

Command ይባላል። በ ሁኔታዎች የማይወሰን ትዕዛዝ ማለት ነው።

🎯 Categorical imperative የ Hypothetical imperative ተቃራኒ ነው። አንድ ነገር ለማግኘት ስንል የግዴታ ማድረግ ያለብን ነገር Hypothetical imperative ነው ብለናል ፤ Categorical imperative ደግሞ ግዴታ ማድረግ ያለብን ነገር ማለት ነው ፤ ድርጊቱን ግዴታ የምናደርገው የሆነ ነገር ለማግኘት ብለን ሳይሆን ግዴታ ማድረግ ስለሚገባን ነው።

📚 ለምሳሌ "አትስረቅ" ፥ "አትዋሽ" ፥ "ሰዎችን አክብር" ፥ "አትዘሙት" ወዘተ እነዚህ ትዕዛዛቶች በሁኔታዎች የማይወሰኑ ትዕዛዛቶች(unconditional command) ናቸው ማለትም Categorical Imperative ናቸው። በሁኔታዎች የማይወሰኑ ትዕዛዛቶች ማለት በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን የግዴታ ልንፈፅማቸው የሚገቡ ትዕዛዛቶች ማለት ነው። በሌላ አባባል የማንሰርቀው ፤ የማንዋሸው ፤ ሰዎችን የምናከብረው ፤ የማንዘሙተው ፤ ቃላችንን የም��ከብረው ወዘተ የሆነ ጥቅም ለማግኘት/ የሆነ ሙገሳ የሆነ ነገር ለማግኘት ብለን አይደለም ፤ የግዴታ ማድረግ ስላለብን ነው። ስለዚህ በሁኔታዎች የማይወሰኑ ትዕዛዛቶችን(Categorical imperative) የምናደርገው የሆነ ነገር ለማግኘት የሆነ ጥቅም ለማግኘት ብለን ሳይሆን ፤ እነዚህን

ትዕዛዛቶች መፈፀም ከሞራል አንፃር ተገቢ ስለሆነ ነው። 🙌ይህን እያለ ያለው Immanuel kant ነው ፤ 😁እኔ አይደለሁም።

🙌 Immanuel kant ታዲያ ድርጊቶችን ትክክል ናቸው ወይም ስህተት ናቸው ብሎ ለመፈረጅ ፤ Hypothetical imperative ወይም Categorical imperative ን ነው የተጠቀመው❓

🙌የ Immanuel kant imperative ... categorical imperative ነው ፤ በሌላ አባባል Immanuel kant አንድ ድርጊት ትክክል ነው ወይም ስህተት ነው ብሎ ለመገምገም የሚጠቀመው Categorical imperative ን ነው። 🙌ፈተና ላይ ስለሚመጣ እንዳትሸወዱ።

የ Immanuel Kant imperative ... categorical imperative ነው ማለት ምን ማለት ነው🤔❓ተመልከቱ ፤ እንደ Immanuel Kant አመለካከት👇

📚 Morality Means acting in accordance with categorical imperative.

🙌 እንደ Immanuel Kant አስተሳሰብ ፤ Morality(ስነ-ምግባር) ማለት  Categorical imperative ን መተግበር ነው። ምን ማለት ነው🤔❓ይኸው👇

📌 An act is <u>moral</u> if it is done in accordance with categorical imperative.
📌 An act is <u>immortal</u> if it is not done in accordance with categorical imperative.

🙌 ተመልከቱ ፧ እንደ ጀርመናዊው የሞራል ፈላስፋ Immanuel Kant አመለካከት👇

📌 አንድ ድርጊት ከሞራል አንፃር ትክክል(moral) ነው የሚባለው ፧ ድርጊቱ categorical imperative ን መሰረት አድርጎ ከተተገበ ነው። Categorical imperative ማለት የሆነ ነገር ለማግኘት ብለን የምናደርጋቸው ትዕዛዛቶች ሳይሆኑ ግዴታ ማድረግ ያለብን በሁኔታዎች የማይወሰኑ ትዕዛዛቶች ናቸው ፧ ማለትም በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን የምንተገብራቸው የምናከብራቸው ፍፁማዊ(absolute) ትዕዛዛቶች ናቸው። "አትዋሽ" የሚለው ትዕዛዝ Categorical imperative ነው። ምንም ይሁን ምን አትዋሽ በቃ አትዋሽ ነው😁። ምንም ይሁን ምን አትስረቅ በቃ አትስረቅ ነው😁። ስለዚህ እንደ Kant ገለፃ በነዚህ የ categorical imperative ህግ መሰረት ድርጊቶችን ስናደርግ ያደረግነው ድርጊት ትክክል(morally right) ነው ይባላል። በአንፃሩ የ categorical imperative ህግን የማያከብሩ ድርጊቶች ደግሞ ፧ ድርጊቶቹ ስህተት(morally wrong) ይባላሉ።

😁 ምሳሌ እንመልከት ፧ "አትዋሽ" የሚለው ትዕዛዝ

በሁኔታዎች የማይወሰን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ልንተገብረው የሚገባ ፍፁማዊ ትዕዛዝ(Categorical imperative) ነው። ስለዚህ እንደ Kant ገለፃ ፤ ይህንን አትዋሽ የሚለውን Categorical imperative መተግበር Morally right ነው ፤ ካልተተገበረ ደግሞ ማለትም 😁ከዋሸን morally wrong ነው። 🙄ታዲያ እስኪ አንድ ታሪክ ልንገራችሁ። አይሁዳውያኖች በ ጀርመኑ መሪ ሒትለር ትዕዛዝ መሰረት እየተለቀሙ በግፍ በጣም በሚያስጠላ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በጥይት ና በኬሚካል ሲገደሉ ነበር😞 ፤ ታዲያ በዛን ወቅት አንድ ጀርመናዊ ሶስት አይሁዳውያኖችን ከቤት ደበቃቸው። ፖሊሶች ከጀርመናዊው ቤት መጥተው እነዛ ሶስት አይሁዳውያን የት እንዳሉ ጠየቁት። እርሱም አላየሁም ብሎ ዋሸ። በመዋሸቱም ሶስቱ አይሁዳውያኖች ከሞት ተረፉ።

🤔 በ Immanuel Kant አስተሳሰብ ጀርመናዊው መዋሸቱ ስህተት ነው ወይስ ትክክል ነው❓መዋሸቱ ስህተት(morally wrong) ነው።

🤔 በ Teleological Ethics አስተሳሰብ ጀርመናዊው መዋሸቱ ስህተት ነው ወይስ ትክክል ነው❓መዋሸቱ ትክክል(morally right) ነው።

ስለ Teleological Ethics ካሁን በፊት በደንብ ስለተማርነው እዚጋ መድገሙ አያስፈልግም። በምሳሌው መሰረት ስለ Kant ግን ትንሽ እንማር🫰።

🙌 በ Kant አስተሳሰብ ፤ ጀርመናዊ ሰው ዋሽቶ ሶስቱን አይሁዳውያን ማዳኑ ስህተት(morally wrong) ነው። ምክንያቱም እንደ Kant አመለካከት አንድ ድርጊት ከሞራል አንፃር ትክክል(moral) ነው የሚባለው ፤ ድርጊቱ categorical imperative ን መሰረት አድርጎ ከተተገበ ነው። Categorical Imperative ማለት ደግሞ ��የትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን የምንተገብራቸው የምናከብራቸው ፍፁማዊ(absolute) ትዕዛዞች ናቸው። በአንፃሩ እነዚህን ፍፁማዊ ትዕዛዞች(absolute command) ያላከበሩ ድርጊቶች ደግሞ ስህተት(morally wrong) ናቸው። ታዲያ👇

እንደ Kant አስተምህሮ ፤ "አትዋሽ" የሚለው ፍፁማዊ ትዕዛዝ ነው። 😁 በቃ አትዋሽ አትዋሽ ነው። በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ሁን ምንም ነገር አግኝ ወይም ምንም ነገር አታግኝ ፤ አትዋሽ ከተባልክ አትዋሽ ነው። ስለዚህ "አትዋሽ" Categorical imperative ነው። ይህንን Categorical imperative የጣሰ ያላከበረ ድርጊት ማለትም መዋሸት morally wrong(ስህተት) ነው። 😁 አያችሁ እንደ kant እሳቤ ጀርመናዊው ዋሽቶ ሶስቱን ሰዎች ማዳኑ ስህተት ነው። ውጤቱ ኮ መልካም ���ው ኣ ፤ ማለትም ሶስቱ አይሁዳውያኖች ከሞት ተርፈዋል። 🤷‍♂️🙅‍♂️ ነገር ግን Deontological Ethics የድርጊቱ ውጤት አያሳስበውም ይልቁንም ድርጊቱ ህግ ና ትዕዛዝን(duty) አክብሯል ወይስ

አላከበረም የሚለው ነው የሚያሳስበው። 😊ስለዚህ ከ Immanuel Kant የ Ethics አስተምህሮ ምን ተረዳችሁ❓በ kant አስተምህሮ አንድ ድርጊት ትክክል ነው የሚባለው ህግና ትዕዛዛትን ሲያከብር ነው ፤ ህግና ትዕዛዛት ማለት ደግሞ duty ማለት ነው። ስለዚህ የ kant ethics በሌላ ስሙ duty based ethics ይባላል።

🙌 የ Kant Ethics ብቻ ሳይሆን ሁሉም የ Deontological Ethics አይነቶች duty based ethics ናቸው። የ deontological ethics አይነቶች እነዚህ ናቸው👇

📌 Divine Command Theory.
📌 Rights Theory.
📌Categorical imperative theory(Kant Ethics)
📌 Prima Facie Duty.

ስለዚህ እነዚህ አራቱ Duty Based Ethics ናቸው። በሌላ አባባል "The means justifies the End" የሚለውን መርህ ይከተላሉ። 👀ፈተና ላይ እንዳትሸወዱ። እንደዚህ ብትጠየቁስ👇

All of the following follows "The means justifies the end" principle except__.

A) Kantism.
B) Rights theory.
C) Divine command theory.

D) Egoism.
E) Utilitarianism.
F) D and E.

🙌 መልሱ F ነው። Utilitarianism ና Egoism የ Teleological Ethics አይነት ናቸው። Teleological Ethics ደግሞ የሚያምነው "The end justifies the means" በሚለው መርህ ነው።

🙌 The end justifies the means ና The means justfies the means ፤ ስለነዚህ በደንብ ስለተማርን እዚህ ላይ መድገም አያስፈልግም። 😁 ወደ Kant እንመለስ ደግሞ።

🙌 እንግዲህ ጀርመናዊው አማኑኤል ካንት የ ድርጊቶችን ሞራላዊ ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት የሚገመግመው በ Categorical imperative(ፍፁማዊ ትዕዛዝ) መርህ ነው። በዚህም ምክንያት የ Kant Ethics ሌላ መጠሪያ ስሙ Categorical Imperative ነው።

🙌 እሺ አሁን ደግሞ የ Kant ን ሶስቱን ቀመሮች(formulas) እንመልከት። ጀርመናዊ Immanuel Kant ከሞራል አንፃር አንድ ድርጊት ትክክል ነው ለማለት ወይም አንድ ድርጊት ስህተት ነው ለማለት ፤ ሶስት ቀመሮችን ወይም መሮሆዎችን ፈልስ��ል። እነርሱም👇

📌 1ኛ) The Principle of Universality(The First Maxim).
📌 2ኛ) The Principle of Humanity as an End.(The Second Maxim).
📌 3ኛ) The Principle of Autonomy.(The Third Maxim).

🙌ሶስቱንም እንመልከት። ይህ A+ Tutorial Class ነው ፤ መምህሩ ደግሞ ዳኒ ነው። ስለ ስነ-ምግባር እየተማራችሁ ፤ ስነ-ምግባር የጎደላችሁ ሞራል የሌላችሁ ብዙ ወፈፌ ፣ ዋልጌ ተማሪዎች አላችሁ የ A+ Tutorial አባል የሆናችሁ። ምን እንደምትሰሩ እናውቃለን ፤ በእናንተ ምክንያት ንፁህ ተማሪዎችን መበደል አንፈልግም ፤ ትምህርቱ ለንፁሀን ብቻ ነው።

🙌ሶስቱን የ Kant ቀመሮች ወይም መርሆዎች ከማየታችን በፊት ፤ Maxim ምን ማለት ነው የሚለውን እንማር።

📚 **<u>Maxim</u>** is **a general truth, fundamental principle, or rule of conduct**.

🎯 Maxim ማለት መሰረታዊ መርህ ወይም የስነ-ምግባር ደንብ ማለት ነው። ለምሳሌ "አትግደል" ፣ "አትስረቅ" ፣ "አትዋሽ" ፣ "ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ" ፣ "ቃልህን ጠብቅ" ፣ "የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ"ወዘተ የመሳሰሉት Maxim ይባላሉ። ስለዚህ Maxim ማለት የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ

ሲኖር በስነ-ምግባር ታንፆ እንዲኖር ለሰው ልጅ የተሰጡ መሰረታዊ የስነ-ምግባር መርህ ፣ ህግ ወይም ትዕዛዝ ማለት ነው።

😁 ታዲያ Immanuel Kant የሰው ልጅ በእያንዳንዱ የህይወት መስመሩ ሊተገብራቸው የሚገቡ ሶስት የስነ-ምግባር ደንቦችን ና ትዕዛዛቶችን(maxim) ቀምሯል ፈልስፏል። ሶስቱንም እንመልከት።

📌**1) The Principle of Universality (The First Formulation)**

🙌 The principle of universality በሌላ ስሙ The First maxim ወይም የመጀመሪያው የስነ-ምግባር መርህ ተብሎ ይጠራል።

🙌 Universality ከስሙ እንደምንረዳው ፤ "**አካታችነት ፣ ሁሉን አቀፋዊነት ፣ ብዙሀንነት ፣ አለም አቀፋዊነት**" የሚል ስያሜ አለው። 🤔 The principle of universality ምን ማለት ነው❓ይህ መርህ የሰው ልጆች ከሚያደርጓቸው ድርጊቶች መካከ�� የትኛው ድርጊት ትክክል ነው ፣ የትኛው ድርጊት ስህተት ነው የሚለውን በምን ቀመር ነው የሚለየው❓ይህ መርህ የሰው ልጆች በስነ-ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ምን አይነት ቀመር አለው❓ የሚሉትን እንማር።

📚 The first maxim states that we should

choose our 'codes of conduct' only if they serve perfect / imperfect duty and are <u>**good for all**</u>.

"Act only according to that maxim whereby you can at the same time will that it should become a universal law without contradiction."

🙌 የመጀመሪያው የ kant የ ስነ-ምግባር ቀመር(first formulation) The principle of universality ነው ብለናል። በዚህ ቀመር መሰረት በአለም ላይ ያሉ ድርጊቶች በሙሉ በ ሁለት ይከፈላሉ። እነርሱም👇

📌1) **Universalizable Action** ( can be universalized).

📌 2) **Non-Universalizable Action**( can not be universalized).

🙌 ስለዚህ በ kant የመጀመሪያው ቀመር መሰረት ፤ universalizable ድርጊቶች አሉ ፤ እንዲሁም ደግሞ non-universalizable ድርጊቶች አሉ።

📚 ታዲያ Immanuel Kant የሚለው ፤ ከሞራል አንፃር universalizable ድርጊቶች ትክክል(morally right) ናቸው ፤ ስለዚህ የ ሰው ልጅ universalizable ድርጊቶችን ነው ማድረግ ያለበት ይላል ካንት። በተቃራኒ�� ደግሞ ፥ ከ

አንፃር non-universalizable ድርጊቶች ስህተት(morally wrong) ናቸው። ስለዚህ የሰው ልጅ non-universalizable ድርጊቶችን በፍፁም ማድረግ የለበትም ይላል ካንት። 🤷‍♂️ በቃ ይህ ነው የካንት የመጀመሪያው የስነ-ምግባር ቀመር። ለመሆኑ universalizable ና non-universalizable ድርጊቶች ምን ማለት ነው 💁‍♀️❓ይኸው👇

📚 Universalizable Action - an action(maxim) someone acts on must be such that others are willing to make it the case that everyone always acts on that maxim when in a similar situation.

📚 Non - universalizable Action - an action(maxim) someone acts on can not be such that others are willing to make it the case that everyone does not act on that maxim when in a similar situation.

🙌 ልብ በሉ ፤ The Principle of Universality ማለት ድርጊቶችን አለምአቀፋዊ ወይም ብዙሀናዊ ማድረግ ማለት ነው። ማለትም አንድ ድርጊት ለማድረግ ስንነሳ ፤ እኔ ያደረኩትን ድርጊት ሌሎች ሰዎች ቢያደርጉትስ ብሎ በማሰብ ድርጊቱን universalize ማድረግ ነው።

📚 በዚህም ምክንያት ድርጊ��ች Universalizable ና Non-unversalizable

ሁሉቱንም እንመልከት።

📌አንድ ድርጊት ለማድረግ ስንነሳ ፤ እኔ ያደረኩትን ድርጊት ሌሎች ሰዎች ወይም አብዛሀኛው ሰው ቢያደርጉትስ ብለን አስበን ፤ ድርጊቱን አብዛሀኛው ሰው ቢያደርገው ጉዳት የማያመጣ ከሆነ ፤ አብዛሀኛው ሰው ድርጊቱን ለማድረግ ፈቃደኛ ከሆነ ፤ ያነ ድርጊት universalizable action ይባላል። አብዛሀኛው ሰው ማለት በአለም ላይ ያሉ ሁሉም ሰዎች ሊሆን ይችላል ፤ በሆነ አካባቢ ያሉ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ ብቻ አብዛሀኛው ሰው በሚለው እንያዘው��

🙌 እስኪ አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ ፤ አንቺ ወደ ትምህርት ቤት እየሔድሽ ነው ፤ አንድ አይነስውር ሰው ጉድጓድ ውስጥ ሊገባ ሲል አየሽው ፤ so ሩጠሽ ሒደሽ አዳንሺው ረዳሺው። 😁 አሁን ያደረግሺውን ድርጊት universalize አድርጊው ፤ ማለትም "እኔ ያደረኩትን ድርጊት ማለትም አይነስውሩን ሰው መርዳት አብዛሀኛው ሰው ሊያደርገው ፈቃደኛ ነው ወይ❓እኔ ያደረኩትን ድርጊት ማለትም አይነስውሩን ሰው መርዳት አብዛሀኛው ሰው ቢያደርገው ጉዳት አለው ወይ❓" ብለሽ ጠይቂ ራስሺን። አብዛሀኛው ሰው ሊያደርገው ፈቃደኛ ነው ፣ ጉዳት የለውም እንደውም ጥቅም አለው።

🙌 ታዲያ ፤ ድርጊቱን አብዛሀኛው ሰው ቢያደርገው ጉዳት የማያመጣ ከሆነ ፤ አብዛሀኛው ሰው ድርጊቱን

ለማድረግ ፈቃደኛ ከሆነ ፤ ያነ ድርጊት universalizable action ይባላል ብለናል።

🙌ስለዚህ አይነስውሩን ሰው መርዳት ወይም Helping the needy ምን አይነት action ነው❓ Universalizable action ነው። ስለዚህ ይህ ድርጊት ትክክል(morally right) ነው ወይስ ስህተት(morally wrong) ነው❓እንደ Kant አስተምህሮ👇

Universalizable action ኖች ከሞራል አንፃር ትክክል ናቸው። ስለዚህ የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት(helping the needy) ማለትም አይነስውሩን ሰው መርዳት universalizable action ስለሆነ ከሞራል አንፃር ትክክል ነው።

እሺ አሁን ደግሞ non-universalizable action ንን እንመልከት።

📌አንድ ድርጊት ለማድረግ ስንነሳ ፤ እኔ ያደረኩትን ድርጊት ሌሎች ሰዎች ወይም አብዛሀኛው ሰው ቢያደርጉትስ ብለን አስበን ፤ ድርጊቱን አብዛሀኛው ሰው ቢያደርገው ጉዳት የሚያመጣ ከሆነ ፤ ያነ ድርጊት non-universalizable action ይባላል።

🙌ለምሳሌ ፤ 😁 ፈተና ነገ ልትፈተን ነው ፤ ከዛ አጤሬራ ይዘህ ለመግባት አሰብክ። 😁እስኪ ያንተን ድርጊት universalize አድርገው ፤ ማለትም "እኔ

የማደርገውን ድርጊት ማለትም አጤሬራ ይዞ መግባት ሁሉም ተፈታኝ ተማሪ ቢያደርገው ምን ይፈጠራል❓" ብለህ ራስህን ጠይቅ። 🙄አስቡት ሁሉም ተፈታኝ ተማሪ አጤሬራ ይዞ ገባ ማለት የሚደርሰው ጉዳት ከባድ ነው።

🙌 ታዲያ ፤ ድርጊቱን አብዛሀኛው ሰው ቢያደርገው ጉዳት የሚያመጣ ከሆነ ፤ ያነ ድርጊት non-universalizable action ይባላል ብለናል።

🙌ስለዚህ ለፈተና አጤሬራ ይዞ መግባት(cheating) ምን አይነት action ነው❓non-universalizable action ነው። ስለዚህ ይህ ድርጊት ትክክል(morally right) ነው ወይስ ስህተት(morally wrong) ነው❓እንደ Kant አስተምህሮ👇

non-universalizable action ኖች ከሞራል አንፃር ስህተት ናቸው። ስለዚህ አጤሬራ ይዞ መግባት non-universalizable action ስለሆነ ከሞራል አንፃር ስህተት ነው። 😂ስለዚህ cheating የሚባለው ነገር ስህተት ነው ፤😕በፍቅረኛችሁ በሚስታችሁ በህይወታችሁ ላይ cheat አታድርጉ❗ ይለናል Immanuel Kant።

🙌ሌላ ምሳሌ ፤ አንተ የመንግስት ባ���ስልጣን ነህ። ጉቦ ለመቀበል አሰብክ። ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ ይልሀል kant.... "🤔 እኔ የማደርገውን

ድርጊት ማለትም ጉቦ መብላትን በአለም ላይ ያሉ ሁሉም ሰዎች ቢያደርጉትስ❓" 🫣 ጉዳቱ በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ non-universalizable action ነው ፤ ከሞራል አንፃር ስህተት ነው።

🙌ስለዚህ እንዴ አማኑኤል ካንት እሳቤ ፤ አንድ ድርጊት ለማድረግ ስናስብ ፤ ድርጊቱን universalize ማድረግ ፤ ማለትም እኔ የማደርገውን ድርጊት ሌሎች ሰዎች ወይም አብዛሀኛው ሰው ወይም በአለም ላይ ያሉ ሰዎች በሙሉ ቢያደርጉትስ ብሎ ማሰብ፤ ታዲያ አብዛሀኛው ሰው ድርጊቱን ���ያደርገው ጉዳት የማያመጣ ከሆነ ድርጊቱ universalizable action ይባላል ፤ ይህ ድርጊት ከሞራል አንፃር ትክክል ነው። አብዛሀኛው ሰው ድርጊቱን ቢያደርገው ና ጉዳቱ የከፋ ከሆነ ድርጊቱ non-universalizable action ይባላል ፤ ይህ ድርጊት ከሞራል አንፃር ስህተት ነው።

😁 ስለዚህ በህይወታችሁ የምታደርጓቸው እያንዳንዶቹ ድርጊቶቹ universalizable action መሆን አለባቸው።

🤷‍♂️ ስለዚህ Principle of univeraslity ማለት ከላይ ያየናቸው ነገሮች ነው።

📚 Kant divides the duties imposed by this formulation into two subsets: perfect and imperfect duty.

🙌 ታዲያ Kant ይህንን የ universality ቀመር ሲቀምር ፤ ግዴታዎች���(duty) በሁለት ከፍሏል። ግዴታ(duty) ማለት ማድረግ የሚገባን ነገር ወይም ማድረግ የሚገባን ድርጊት ማለት ነው። እንደ Kant አስተምህሮ ፤ ግዴታ(duty) በሁለት ይከፈላሉ👇

1) Perfect Duty(ፍፁማዊ ግዴታ)
2) Imperfect Duty(ፍፁማዊ ያልሆነ ግዴታ)

ሁለቱንም እንመልከት።

�� Perfect duties are blameworthy if not met and are the basic requirements for a human being.

🎯 ፍፁማዊ ግዴታዎች(Perfect duties) የ ሰው ልጅ ሊያደርጋቸው የሚገቡ መሰረታዊ የስነ-ምግባር መርሆዎች ሲሆኑ እነዚህን ፍፁማዊ ግዴታዎች አለማድረግ ደግሞ ተወቃሽነትን ቅጣትን ያስከትላሉ። ስለዚህ እንደ kant አስተምህሮ non-universalizable action ኖችን ያለማድረግ ፍፁማዊ ግዴታ አለብን ወይም universalizable action ኖችን የማድረግ ፍፁማዊ ግዴታ አለብን👇

📌 According to his reasoning, we first have a perfect duty not to act by maxims that result in logical contradictions when we attempt to universalize them.

🤔 not to act by maxims that result in logical contradictions when we attempt to universalize them ምን ማለት ነው❓ይኸው 👇

አንድ ድርጊት ለማድረግ ስንነሳ ፤ እኔ ያደረኩትን ድርጊት ሌሎች ሰዎች ወይም አብዛሀኛው ሰው ቢያደርጉትስ ብለን አስበን ፤ ድርጊቱን አብዛሀኛው ሰው ቢያደርገው ጉዳት የሚያመጣ ከሆነ ፤ ያነ ድርጊት non-universalizable action ይባላል። ስለዚህ Non-universalizable action ኖችን ያለማድረግ ፍፁማዊ ግዴታ(perfect duty) አለብን።

🙌 ለምሳሌ ፤ መስረቅ ፥ መዋሸት ፥ ማጭበርበር ፥ መግደል ወዘተ Non-universalizable action ናቸው።

ስለዚህ እነዚህን non-universalizable action ኖችን ያለማድረግ ፍፁማዊ ግዴታ(perfect duty) አለብን ማለትም አለመስረቅ ፣ አለመዋሸት ፣ አለማጭበርበር ፣ አለመግደል ወዘተ ፍፁማዊ ግዴታችን ነው። 🙌 ታዲያ እነዚህን ፍፁማዊ ግዴታዎች በአግባቡ ካልተወጣን ደግሞ blameworthy ነው ማለትም ተወቃሽ ተጠያቂ ተቀጪ እንሆናለን። 🙄ህግ እንኳን ባይቀጣን ህሊናችን ይቀጣናል።

🤔 ስለዚህ ከ Perfect duty ምን ተረዳችሁ❓
Perfect duty ማለት ማድረግ ያለብን ፍፁማዊ ግዴታዎች ወይም ማድረግ የሌለብን ፍፁማዊ ግዴታወች ማለት ነው ፤ እነዚህን ግዴታዎች ካላሟላን ተጠያቂነት ተወቃሽነት ያስከትላል። ለምሳሌ ፤ ራስን ማጥፋት(suicide) ማድረግ የሌለብን ፍፁማዊ ግዴታ ፤ እውነትን መናገር ማድረግ ያለብን ፍፁማዊ ግዴታ ነው።

✌️ Perfect duty subjective አይደሉም። subjective ማለት ከ ሰው ሰው የሚለያይ ማለት ነው። perfect duty ዎች ከሰው ሰው አይለያዩም ፤ ሁሉም ሰው ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ለሁሉም ሰው እኩል የሆኑ ፍፁማዊ ግዴታዎች ናቸው። አለመስረቅ ፤ አለመግደል ፤ አለመዋሸት ፤ የተቸገሩትን መርዳት ወዘተ ሁሉም ሰው ሊያደርጋቸው የሚገቡ ፍፁማዊ ግዴታዎች ና���ው። 😁 አበበን አትስረቅ ፤ ከበደን ስረቅ የሚል ትዕዛዝ የለም። አትስረቅ ለሁሉም ሰው የሚሰራ maxim ነው።

�� <u>Imperfect duti</u>es are those that do not achieve blame, rather they receive praise if completed; they are circumstantial duties such as cultivating talent.

📌 Because these depend somewhat on the subjective preferences of humankind, this duty is not as strong as a perfect

duty, but it is still morally binding.

📌 As such, unlike perfect duties, you do not attract blame should you not complete an imperfect duty but you shall receive praise for it should you complete it.

✌️ imperfect duty ማለት ደግሞ ፍፁማዊ ያልሆነ ግዴታ ማለት ነው። የ perfect duty ተቃራኒ ማለት ነው።

✌️ ፍፁማዊ ያልሆኑ ግዴታዎች(imperfect duty) በርግጥ ግዴታዎች ናቸው ነገር ግን እነዚህን ግዴታዎች ባንፈፅማቸው ባንተገብራቸው ባንወጣቸው እንኳን ተወቃሽነት ፥ ቅጣት አያስከትሉም ነገር ግን እነዚህን ግዴታዎች ብንተገብራቸው ግን ምስጋናን አድናቆትን ያስገኛሉ ፤ ለ imperfect duty ጥሩ ምሳሌ ተሰጥኦ(talent)ን ማዳበር ነው ፤ 😁 ተሰጥኦኣችንን ማዳበር ማሳደግ ፍፁማ ያልሆነ ግዴታ ነው ማለትም ተሰጥኦችንን ብናዳብር መልካም ነው ሽልማት አድናቆት ተፈላጊነት እናገኝበታለን ነገር ግን የ ግዴታ ግዴታ አይደለም ፤ ማለትም ተሰጥኦኣችንን ባናዳብር እንኳን አንወቅስም አንቀጣም። 😁ለምሳሌ አንድ ሰው ኳስ የመጫወት ተሰጥኦ ቢኖረው ና ግን ኳሱን ትቶ ትምህርቱን ቢማር ለምን ኳስ ተጫዋች አልሆንክም ተብሎ የሚጠየቅበት ህጋዊ አካሄድ የለም።

✌️አያችሁ ኣ perfect ና imperfect duty ተቃራኒ ናቸው። ይኸው👇

👉 ፍፁማዊ ግዴታዎች(perfect duty) ን ካልተወጣናቸው ካልተገበርናቸው ቅጣትን ተወቃሽነትን ያስከትላሉ።
👉 ፍፁማዊ ያልሆኑ ግዴታዎችን(imperfect duty) ን ካልተገበርናቸው ካልተወጣናቸው ቅጣትን ተወቃሽነትን አያስከትሉም።
👉 ፍፁማዊ ግዴታዎች(perfect duty) ን ብንተገብራቸው ሽልማት አድናቆት አያሰጡም ምክንያቱም በህይወት ስንኖር ማድረግ የሚገቡን ግዴታዎች የህይወት መ��ሆች ናቸው። አለመስረቅ አለመግደል አያሸልምም ኣ። 🤷‍♂️ ህሊና ና ሞራል እስከተሰጠን ድረስ እንዲሁ ማድረግ የሚገባን ግዴታ ነው።
👉 ፍፁማዊ ያልሆኑ ግዴታዎች(perfect duty) ን ብንተገብራቸው ሽልማት አድናቆት ያሰጣሉ። ለምሳሌ ተሰጥኦችንን ብናዳብር አድናቆት ሽልማት እናገኛለን😁ሜሲ ለምሳሌ።

👉 Perfect duty ዎች circumstantial አይደሉም ፤ ማለትም በሁኔታዎች የሚወሰኑ አይደሉም። በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን በቋሚነት ልንተገብራቸው የሚገቡ ፍፁማዊ ግዴታዎች ናቸው። ለምሳሌ ራስን አለማጥፋት በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ልንተገብረው የሚገባ ፍፁማዊ ግዴታ ነው። 😏ግሬድ ወረደብኝ

ከአስተማሪ ጋ ተጣላሁብኝ ፍቅር ያዘኝ ብላችሁ ራሴን ካለጠፋሁ የምትሉ ልጆች ፤ ይህንን ፍፁማዊ ግዴታችሁን አስተውሉ😁 ካንት ነው ያለው እኔ አይደለሁም።

👉 imperfect duty ዎች circumstantial ናቸው ፤ ማለትም በሁኔታዎች ውስጥ የሚወሰኑ ናቸው። 😁ሁኔታዎች ካልተመቻቹልን ነገሮች ካልተመቻቹልን መተው እንችላለን የግዴታ ማድረግ አይጠበቅብንም ፤ ሁኔታዎች ከተመቻቹ ግን ብናደርጋቸው አድናቆት ና ሽልማት ያስገኛሉ። ስለዚህ imperfect duty ን በቋሚነት(constantly) ላንተገብረው እንችላለን ማለትም እንደሁኔታው ይወሰናል። ለዛም ነው **Imperfect duties are circumstantial, meaning simply that you could not reasonably exist in a constant state of performing that** duty የተባለው።

✌ Perfect duty ግን Circumstantial አይደሉም። ማለትም በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብሆን ፤ 😁በከፍታም ብንኖር በዝቅታም ብንኖር የግዴታ መተግበር የሚገባን ነው። በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን መስረቅ የለብንም ፣ መግደል ፣ መዋሸት ወዘተ የለብንም። ስለዚህ perfect duty ዎችን ሁኔታዎች ሳይወስኑን በቋሚነት(constantly) የምንተገብራቸው ናቸው።

👉 Perfect duty ዎች subjective አይደሉም ፤

Objective ናቸው። ማለትም ለሁሉም ሰው እኩል የሚሰሩ ናቸው። አለመስረቅ perfect duty ነው ፤ አለመስ���ቅ ሁሉም ሰው ሊተገብረው የሚገባ ለሁሉም ሰው የተሰጠ ፍፁማዊ ትዕዛዝ ነው።

👉 Imperfect duty ዎች Subjective ናቸው። ማለትም ከሰው ወደ ሰው ይለያያሉ። ተሰጥኦን ማዳበር ፍፁማዊ ያልሆነ ግዴታ(imperfect duty) ነው ብለናል። የእያንዳንዱ ሰው ተሰጥኦ ይለያያል ፤ ስለዚህ ተሰጥኦን ማዳበር ከሰው ሰው ይለያያል ስለዚህ subjective ነው ማለት ነው። ለአንዱ ጥሩ መናገር ተሰጥኦ ነው ፤ ለሌላኛው መተወን ተሰጥኦ ነው ፣ ለሌላኛው የ ፈጠራ ስራ ተሰጥኦ ነው ወዘተ።

👉 Perfect duty ዎች የግዴታ ግዴታ ሲሆኑ ፤ በአንፃሩ ደግሞ imperfect duty ዎች የውዴታ ግዴታ ናቸው። ✌️ተንትኑት።

✌️ ከ perfect duty ና ከ imperfect duty የትኛው ነው strong duty❓ተንትኑት። ከላይ አይተንዋል ሁሉን��።

🙌 ስለ Principle of universality ከዚህ ላይ እናብቃ ና ሁለተኛውን የካንት ቀመር እንመልከት።

📌 **B) The Principle of Humanity as an End, Never as Merely a Means.**

📚The second maxim states that we

should not use humanity of ourselves or others as a means to an end.

🎯 **<u>“Act in such a way that you treat humanity, whether in your own person or in the person of any other, never merely as a means to an end, but always at the same time as an end.”</u>**(ይህ የህይወታችን መርህ ሊሆን ይገባል።)

📌 Every rational action must set before itself not only a principle, but also an end.

📌 This principle has received more widespread approval than any other part of Kant’s moral philosophy.

📌 People, as rational beings, are ends in themselves and should never be used merely as means to other ends.

📌 We may use physical things as means, but when we use people simply as means, as in slavery, prostitution, or commercial exploitation, we degrade them and violate their innermost beings as people.

🙌 ሁለተኛው የካንት ቀመር ዋና መልዕክቱ ፤ " **<u>በህይወታችሁ የምታደርጉት እያንዳንዱ ድርጊት የሰውን ልጅ ክብር ባስቀደመ መልኩ መሆን አለበት</u>**"

ነው የሚለው።

😁 ይህ ቀመር ለ ሰው ልጆች ልዩ አክብሮት ና ድጋፍ ይሰጣል። ጀርመናዊው ካንት "**<u>የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጥረቶች የተለየ ክቡር ና ድንቅ ፍጡር ነው</u>**" ይላል። ታዲያ እንደ ካንት አስተምህሮ👇

🙏 ለራሳችን ጥቅም ሲባል ፤ ለራሳችን ድሎት ና ምቾት ሲባል ሌሎች ሰዎችን እንደ ግብአት መጠቀም ፣ ሌሎች ሰዎችን የራስ መጠቀሚያ ማድረግ ፣ መበዝበዝ የለብንም።

🙏ስለዚህ በህይወታችን የምናደርጋቸው ድርጊቶች በሙሉ የሰው ልጆችን ባከበረ መልኩ መሆን አለበት እንጂ ፤ ለራስ ጥቅም ሲባል ሰዎችን መጠቀሚያ(ግብአት) ማድረግ የለብንም።

🙌 ታዲያ ፤ ለራስ ጥቅም ���ባል ሌሎች ሰዎችን እንደ ግብአት መጠቀም ወይም ሌሎች ሰዎችን መጠቀም መበዝበዝ Means ይባላል።

🙌 የሰው ልጆች ደግሞ በተፈጥሯቸው End ናቸው። ማለትም ከሰው ልጆች የሚበልጥ ሌላ ምንም ነገር የለም ማለት ነው። የመጨረሻው ትልቁ(End) የሰው ልጅ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ከሁሉም የላቀ ከምንም የሚበልጥ ክቡር ፍጡር ነው።

🙌 በአንፃሩ ደግሞ፣ ሰዎችን በዝብዞ ሰዎችን

አለአግባብ ተጠቅሞ የራስን ፍላጎት ማርካት የራስን ጥቅም ማስፈፀም ሌላ End ነው።

🙌 Humanity ማለት ደግሞ የሰው ልጅ ወ���ም ሰው ማለት ነው።

😁 ታዲያ ካንት ከነዚህ means ና End በመነሳት ፣ ቀመር ቀመረ። ይኸው👇

<u>Treat humanity as an End, not as merely a mea</u>ns.(ያዙት ፈተና ላይ ይወጣል)።

🙌 ስለዚህ ቀመሩ ምን መሰላችሁ የሚለው ፤ የሰው ልጅ በተፈጥሮው End ነው ፤ ማለትም ከሰው ልጅ የሚበልጥ ሌላ ነገር የለም የሰው ልጅ የመጨረሻው(end) ትልቁ ክቡር ፍጡር ነው። የሰው ልጅ በራሱ End ነው ስለዚህ ለሌላ End ማለትም ለሌላ የራስ ጥቅም የሰው ልጅን እንደ ግብአት(means) መጠቀም የለብንም። ነው የሚለው ካንት።

🎯 ስለዚህ ሁለተኛው የካንት ቀመር የሚለው ፤ የሰው ልጃ የመጨረሻው ትልቁ ክቡር ፍጡር ነው ከሰው ልጅ የሚበልጥ የለም ና የምናደርጋቸው እያንዳንዱ ድርጊቶች የሰውን ልጅ ክ��ር(End) ባስቀደመ መልኩ መሆን አለበት እንጂ ለራሳችን ጥቅም(other end) ሰዎችን እንደ ግብአት መጠቀም(means) የለብንም ማለትም ሰዎችን

መጠቀሚያ ማድረግ መበዝበዝ ተገቢ አይደለም። ከሰው ልጅ የሚበልጥ የለም፤ ስለዚህ የሰው ልጅ ግብአት(means) አይደሉም ይልቁንም የመጨረሻው(end) ትልቅ ክቡር ፍጡር ናቸው። ስለዚህ👇

የሰው ልጆች(humanity)ን as a means ሳይሆን as an End ነው treat ማድረግ ያለብን። True/ false ፈተና ላይ እንዲህ ተብላችሁ ብትጠየቁስ 👇

The central point of categorical imperative is treating of human beings as a means to your own end.

😎 False ነው ኣ።

😊 ከሶስቱ የካንት ቀመሮች ይህ ቀመር በብዙዎች ዘንድ ተወዳጅነት ና ተቀባይነት አግኝቷል ምክንያቱም ለሰው ልጅ ትልቅ ክብር ስለሚሰጥ። በተለይም በባርነት ፣ በሴተኛ አዳሪነት ፣ በቤት ሰራተኝነት ፣ በጉልበት ብዝበዛ ሰዎችን ለራሳቸው ጥቅም እንደ ግብአት የሚጠቀሙ አካላትን አጥብቆ ይቃወማል።

📌 The categorical imperative also regulates the morality of actions that affect us individually. For example, Suicide would be wrong since I would be treating my life as a means to the alleviation of my misery.

🙌 ይህ ቀመር ፤ ለራሳችን ጥቅም ሲባል ፣ ለራሳችን የሆነ ነገር ለማግኘ�� ሲባል ሌሎች ሰዎችን የመስዋዕት በግ ማድረግ የለብንም ብቻ አይደለም የሚለው ፤ ለራሳችን የሆነ ነገር ለማግኘት ሲባል ራሳችንን የመስዋዕት በግ ማድረግ የለብንም ይላል። ለምሳሌ👇

🙌 ለምሳሌ "አንድ ሰው ችግር መከራ ቢደራረብት ና ከዚህ ችግሩ ለመውጣት ራሱን ቢያጠፋ ስህተት ነው" እንደዚህ ቀመር። ምክንያቱም ከችግሩ ለመላቀቅ(end) ራሱን እንደ ግብአት(means) ነው የተጠቀመው። ስለዚህ suicide wrong ነው።

ስናጠቃለው ፤ የካንት ሁለተኛው ቀመር መሰረታዊ መልዕክት👇

📌 We should always treat people with dignity, and never use them as mere instruments. For Kant, we treat people as an end whenever our actions toward someone reflect the inherent value of that person.

ጀርመናዊው ካንት እንዲህ ብሎ ይመክረናል����

🎯 ሰዎችን ሁል ጊዜ በአክብሮት ልንይዛቸው እንጂ እንደ ተራ መሣሪያ ልንጠቀምባቸው አይገባም። እንደ ካንት አስተምህሮ፣ በአንድ ሰው ላይ የምናደርጋቸው

ድርጊቶች የዚያን ሰው የተፈጥሮ እሴት ክቡርነት(inherent value) የሚያንፀባርቁ መሆን አለባቸው። ማለትም ሰዎችን ለራሳችን ጥቅም እንደ ግብአት(means) መጠቀም ሳይሆን ሰው መሆናቸውን ክቡርነታቸውን(end) በሚመጥን መልኩ ልንቀርባቸው ልንይዛቸው ይገባል።

✌️በአጭሩ የ ካንት መልዕክት ፤ ሰዎችን ለጥቅማችሁ ብላችሁ አትቅረቡ። እንደ ሰውነታቸው ቅረቧቸው እንጂ።

🙌 **Treating Humanity as an End, never as merely a Means.** ማለት ይህ ነው።👏👏 እስኪ አንድ ጊዜ ለካንት።

✌️ስለዚህ **Treating Humanity as an End** በሁኔታዎች የሚወሰን አይደለም ፣ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ልንተገብረው የሚገባ ነው ፤ ከሰው ሰው አይለያይም፤ስለዚህ subjective ሳይሆን objective ነው።

🙌 ሞጁሉ ላይ ያለውን አሰስ ገሰስ ለመያው ዝ አትሞክሩ ፤ ዋና ሀሳቡን ብቻ ተረዱት። ፈተና የሚወጣው ዋና ሀሳቡ ነው እንጂ detail የሆነ ነገር ስለማትጠየቁ ሞጁሉ ላይ ያለውን ኖት በፍፁም እንዳትሸመድዱ ፤ ዋና ሀሳቡን ብቻ ተረዱ።

3ተኛውን ቀመር ና prima facie duty በቀጣይ

እናያለን።

This Tutorial is prepared by Daniel Elias of The A+ Tutorial Class.

© A+ Tutorial Class.